**ታህሳስ /2013 ዓ.ም**

# የፍልሰት ብሔራዊ የትብብር ጥምረት አባላትንና የሥራ ቡድኖችን አደረጃጀት እና አሰራር ለመወሰን የተዘጋጀው ረቂቅ መመሪያ ማብራሪያ

## መግቢያ

በሰው የመነገድ፣ ሰውን በህገወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር እና ሰውን ለስራ በህገወጥ መንገድ ወደ ውጭ አገር የመላክ ወንጀሎች በተደራጀ፣ ውስብስብና ረቂቅ በሆነ መንገድ የሚፈፀሙ የሰው ልጆችን ሰብአዊ መብቶች በመጋፋት ለከፍተኛ ስቃይና እንግልት ከማዳረግም ባለፈ እስከ ሞት የሚደርስ ጉዳትን ሊያስከትሉ የሚችሉ አደገኛነታቸውና አሳሳቢነታቸው በአለም ደረጃ እየጨመረ የመጣ የወንጀል አይነቶች በመሆናቸው ወንጀሎቹን ለመከላከልና የሚያስከትሉትን ጉዳት ለመቀነስ የአገራትን ቁርጠኝነትና ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቁ የወንጀል አይነቶች መሆናቸው የማያጠያይቅ ጉዳይ ነው፡፡ ወንጀሎቹን ለመከላከልና ሊያስከትሉ የሚችሉትን ጉዳት ለመቀነስ ብሎም ለማስቀረት ከሚያስችሉ ስልቶች መካከል ጠንካራ የህግ ማዕቀፍ መኖር፣ የተደራጀና ወጥነት ያለው የትብብር፣ የቅንጅት እና የህግ ማስከበር ተግባር፤ እንዲሁም ተጎጂዎችን መልሶ የማቋቋም ስራ በአግባቡ የሚሰራበትን ስርዓት ማዘርጋት አስፈላጊ እርምጃዎች ናቸው፡፡

በዓለማቀፍ ደረጃ የተደራጁና ድንበር ዘለል ወንጀሎችን ለመከላከል በ2000(እ.ኤ.አ) የተደረገ ስምምነት እንዲሁም ይህን ስምምነት የሚያሟሉ በተመሳሳይ ዓመት በሰዎች መነገድ በተለይም የሴቶችና ሕጻናት ዝውውር ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ወንጀል ፈጻሚዎችን ለመቅጣት እና ሰዎችን በሕገ-ወጥ መንገድ በየብስ፣ በባህርና በአየር ማስወጣትና ማስገባት ለመከላከል የወጡ ፕሮቶኮሎች ተፈርመዋል፡፡ ኢትዮጵያም ወንጀሎቹን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እነዚህን ስምምነቶችን በመቀበል እንደቅደም ተከተላቸው በአዋጅ 526/1999፣737/1999 እና 736/1999 በማጽደቅ ማስፈጸሚያ ህጎችን በማውጣትና በማሻሻል ስትተገብር ቆይታለች፣ እየተገበረችም ትገኛለች፡፡

በመሆኑም አሁን በመተግበር ላይ የሚገኘው በሰው የመነገድ እና ሰውን በህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 1178/2012 ቀድመው ከነበሩት ህጎች በተሻለ ሁኔታ ወንጀሎቹን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አስተዋጽኦ እንደሚኖረው የሚታመን ቢሆንም ወንጀሎቹን በተገቢው ሁኔታ ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ለተጎጅዎች ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግና መልሶ የማቋቋም ስራ ለመስራት ከፍተኛ የሆነ ቅንጅታዊ ስራን የሚጠይቅና የተለያዩ አደረጃጀቶችን እና አሠራሮችን መፍጠርና ማዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 35(1) መሰረት የአዋጁን ተፈጻሚነት የሚያስተባብር ብሄራዊ የትብብር ጥምረት ተቋቁሟል፡፡

ስለሆነም አዋጁ ተተግብሮ ዓላማውን እንዲያሳካ የብዙ ባለድርሻ አካላትን ቅንጅታዊ ሥራ የሚጠይቅ እንደመሆኑ ማጠን የትብበር ጥምረቱን አደረጃጀት እና አሰራር የሚወስን መመሪያ በማውጣት ጸድቆ ወደ ሥራ እንዲገባ ማድረግ በማስፈለጉ ረቂቅ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## የረቂቅ መመሪያው አስፈላጊነት

በሰው የመነገድና ሰወን በህገወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 1178/2012 ከተቋቋሙት አደረጃጆቶች መካከል ብሄራዊ የትብበር ጥምረት ነው፡፡ ጥምረቱበጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የሚመራ ሆኖ ተጠሪነቱ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ለሚመራው ብሄራዊ ምክር ቤት ነው፡፡ የትብበር ጥምረቱ የተለያዩ መንግስታዊ ተቋማትን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን፣ የሀይማኖት ተቋማትን ያካተተ ሲሆን የውስጥ አደረጃጀቱና አሠራሩ ብሄራዊ ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ እንደሚወስን በአዋጁ አንቀጽ 35(5) ሥር ተደንግጓል፡፡

በመሆኑም አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ የትብበር ጥምረቱ አደረጃጀት አሠራር መወሰን ቀዳሚ ቁልፍ ተግባር በመሆኑ ይህን ረቂቅ መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፤

## የረቂቅ መመሪያው አደረጃጀት

መመሪያው በአጠቃላይ 3(ሦስት) ክፍሎችን እና 23 (ሀያ ሦስት) አንቀፆችን እንደኖሩት ተደርጎ የተዘጋጀ ሲሆን ክፍል አንድ የመመሪያወን ጠቅላላ ድንጋጌ (አንቀጽ 1 "አጭር ርዕስ" ፣ አንቀጽ 2 የቃላትና ሃረጋት "ትርጓሜ"ን እና አንቀጽ 3 ደግሞ "ተፈጻሚነት ወሰን"ን ይይዛል፡፡

የረቂቅ መመሪያው ክፍል ሁለት በአጠቃላይ የብሔራዊ ትብብር ጥምረቱን አባላት ዝርዝር፣ አደረጃጀትና አሠራርን የሚወስኑ ድንጋጌዎችን የሚያጠቃልል ሲሆን ሁለት ንዑስ ክፍልሎችን ይዟል፡፡ ንዑስ ክፍል አንድ የብሔራዊ ትብብር ጥምረቱን አባል ተቋማት(አንቀጽ 4) እና በትብብር ጥምረቱ ሥር የተደራጁ የስራ ቡድኖችን (አንቀጽ 5) የሚሸፍን ሲሆን ንዑስ ክፍል ሁለት ደግሞ ስለ ብሄራዊ የትብብር ጥምረቱ የስራ ቡድኖች የወልና የተናጠል ኃላፊነት፣ አሠራር፣ የየስራ ቡድን ሠብሳቢዎች ተግባርና ኃላፊነት እና ስለጥምረቱ የስብሰባ ጊዜ የሚወስኑ ድንጋጌዎችን ይሸፍናል፡፤

የረቂቅ መመሪያወ የሚጨረሻ ክፍል (ክፍል ሦስት) ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን ከአንቀጽ 21 እስከ አንቀጽ 23 ያሉትን የሚጨረሻ ድንጋጌዎች ይይዛል፡፡

## ዝርዝር ማብራሪያ

የረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 1 የመመሪያወን አጭር ርዕስ(ማጠሪያ ስያሜ) የያዘ ሲሆን መመሪያው በአጠቃላይ የትብብር ጥምረቱ በአዋጁ ከተሰጠው ኃላፊነት ሥልጣና አዋጁ ሊያሳካ ከፈለገው ዓላማ ማለትም ወንጀሎቹን ለመከላከል ለመቆጣጠር ፍለሰትን በአግባቡ ማስተዳደር እና መደበኛ የፍልሰት አማራጭ የሰዎች ቀዳሚ ምርጫ እንዲሆን በማስቻል ሰዎች ለወንጀሉ ያላቸወን ተጋላጭነት መቀነስ፣ ወንጀሉ ተፈጽሞ ሲገኝ ደግሞ አጥፊዎችን ለህግ ማቅረብና ተጎጂዎችን መደግፍና ማቋቋም በመሆኑ ሥያሜው ከፍልሰት አስተዳደር አንጻር ቢቃኝ ገላጭ ይሆናል በማለት "የፍልሰት ብሔራዊ የትብብር ጥምረት አባላትንና የሥራ ቡድኖችን አደረጃጀት እና አሰራር ለመወሰን የወጣ መመሪያ" የሚል ሥያሜ እንዲሰጠው ተደርጓል፡፡

ረቂቅ መመሪያው **አንቀጽ 2** በመመሪያው ወስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሀረጋት በመመሪያው አተገባበር ላይ የሚኖራቸወን ትርጉም ያስቀመጠ ነው፡፡ ይህ አንቀጽ 4 ንዐስ አንቀሶችን የያዘ ሲሆን በአንቀጽ2(1) አዋጅ ማለት አዋጅ ቁጥር 1178/2012 እንሆነ፣ ብሄራዊ የትብብር ጥምረት ማለት በአዋጁ አነቀጽ35(1) ማስረት የተቋቋመው ጥምረት እንደሆነ እና ፍልሰት ማለት ደግሞ መደበኛና መደበኛ ባልሆነ መንገድ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚደረግ የሰው ወይም የሰዎች እንቅስቃሴ ማለት እንደሆነና ስደተኞችን፣የተፈናቀሉ ሰዎችን፣ የኢኮኖሚ ፍልሰተኞችን እና ሌሎችን እንዲሚያጠቃልል ተደጎ ተተርጉሚል( አንጽ 2/3)፡፡ አንቀጽ 2(4) ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 2 እና በፍልሰት ጉዳዮች ላይ በወጡ ሌሎች አዋጆች፣ደንቦችና መመሪያዎች የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደየአግባብነታቸው ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ተደንግጓል፡፡

የረቂቅ መመሪያው **አንቀጽ 3** የመመሪያወን የተፈጻሚነት ወሰን የሚደነገግ ሲሆን በብሔራዊ የትብብር ጥምረቱና አባላት፤ ብሄራዊ የትብብር ጥምረቱ ሥር በተደራጁ የስራ ቡድኖች፣ ንዐስ የስራ ቡድኖች እና ሌሎች በፍልሰት ጉዳዮች ላይ በህግ ተግባር እና ኃላፊነት በተሰጣቸው አካላት እና አደረጃጀቶች ላይ ተፈጻሚነት እንዲኖር ተደርጓል፡፡

አንቀጽ 4 የትብብር ጥምረቱን አባል ተቋማት ዘርዝሮ ያስቀምጠ ድንጋጌ ነው፡፡በአዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 33(3) ሥር የብሄራዊ ምክር ቤቱ አባል ተቋማት ተዘርዝረው ይገኛሉ፡፡በዚህ ድንጋጌ በግልጽ ከተደዘረዘሩት በተጨማሪ ሌሎች ተቋማትም በምክትል ጠ/ሚኒስቴሩ ወሳኔ እንዲካቱ ሊደረግ እንደሚቻል ተመልክቷል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 35(3) ማስረት እነዚህ ተቋማት ከክልሎች በስተቀር የብሄራዊ የትብብር ጥምረቱ አባል ይሆናሉ፡፡ በዚህ ማስረት ይህ መመሪያ በብሄራዊ ምክር ቤቱ የሚጸድቅ እንደመሆኑ እና ምክረ ቤቱ ደግሞ የሚመራው በምክትል ጠቅላይ ሚኒሰቴሩ በመሆኑ በአዋጁ ከተዘረዘሩት አባል ተቋማት በተጨማሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒሰቴሩ በምክር ቤቱ ወሳኔ አማካኝነት እንዲያካትታቸው በማሰብ ሌሎች ተቋማት በረቂቅ መመሪያው እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

ስለሆነም ብሔራዊ የትብብር ጥምረቱ በአዋጁ አንቀጽ 33(3) ሥር የተዘረዘሩት አባላቱ እንደተጠበቁ ሆነው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር፣የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ግብርና ሚኒስቴር፣የፕላንና ልማት ኮሚሽን፣የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የፌደራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ማስፋፊያ

ባለስልጣን፣የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን፣የኢምግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች አጀንሲ፣የፌደራል ከተሞች ስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ፣የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ፣የብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን፣የተባበሩት መንግስታት የአደንዛዥ ዕጽ እና ወንጀሎች መቆጣጠሪያ ቢሮ፣የዓለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት፣የዓለም የሥራ ድርጅት፣የተባበሩ መንግስታት ከፍተኛ የስደተኞች ኮሚሽን፣የተባበሩት መንግስታት የህጻናት መርጃ ድርጅት፣የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሳይንስና የከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር፣የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተወካይ፣የኢትዮጵያ የሐይማኖት ተቋማት ጉባኤ እና ሌሎች በብሄራዊ ም/ቤቱ ሰብሳቢ እንዲካተቱ የሚደረጉ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን እንዲያካትት ሆኖ ተደርጎ ተደንግጓል፡፡ የጥምረቱ አባል ተቋማት በየተቋሞቻቸው አግባብነት ያላቸው ምክትል ሃላፊዎችን በአባልነት መመደብ እንዳለባቸው በአንቀጽ 4(4) ሥር ተደንግጓል፡፡

በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 5 ሥር የብሄራዊ የትብብር ጥምረቱ የስራ ቡድኖች ተደራጅተዋል፡፡ የትብብር ጥምረቱ በአዋጁ የተደነገጉ ወንጀሎችን መከላከልና መቆጣጠር የሚቻለው ትክክለኛ የፍልሰት አስዳደር ሲኖር ማለት ፍልሰትን በአግባቡ በማስተዳደር የወንጀል ተጋላጭነትን በመቀነስ እና ከፍለሰት የሚገኙ ጥቅሞችን ደግሞ በአግባቡ በማጠቀም ሚቀፍ ወስጥ ነው ብሎ በማመን የሥራ ቡድኖቹ በዚህ ቅኝት ተደራጂተዋል፡፡

በዚህም ማሰረት የትብብር ጥምሩ የግንዛቤ ፈጠራና የባህሪይ ለውጥ እና የውጭ ሐገር ሥራ ሥምሪትና ልማት የስራ ቡድን፣ የወንጀል መከላከል እና የህግ ማስከበር የስራ ቡድን፣ የተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የስራ ቡድን፣ የዳያስፖራ ተሳትፎና ልማት ጉዳይ የስራ ቡድን፣ የፍልሰት መረጃና አስተዳደር የሥራ ቡድን እና የጥናትና ምርምር የስራ ቡድን የተባሉ 6 የሥራ ቡድኖች እንዲኖሩት ተደርጎ በአንቀጽ 5(1) ተደንግጓል፡፡

በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 6 ሥር የግንዛቤ ፈጠራና የባህሪ ለውጥ እና የውጭ ሀገር ስራ ስምሪትና ልማት የስራ ቡድን አባላትን በመዘርዘር ያስቀመጠ ሲሆን እነሱም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰብሳቢነት የሚመሩ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣የስራ እደል ፈጠራ ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ፣የፌደራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ፣የኢምግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት አጀንሲ፣ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ፣የኢትዮጵያ ሴቶች ፌዴሬሽን፣የኢትዮጵያ ወጣቶች ፌዴሬሽን፣የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፣የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበራት ኮንፌደሬሽን፣የኢትዮጵያ አሰሪዎች ፌዴሬሽን፣የፋና ብሮድካስት ኮርፖሬሽን፣የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን፣ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ኤጀንሲ፣ዋልታ ሚዲያ እና ኢንፎርሜሽን ማእከል፣የጀርመን የልማት ተራድኦ ድርጅት፣የኢትዮጵያ ሀይማኖት ተቋማት ጉባኤ ፣የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር፣የክርስትያን በጎ አድራጎትና ልማት ማህበር ፣የዓለም የሥራ ድርጅት፣የዓለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት፣የተባበሩት መንግስታት የአደንዛዥ ዕጽ እና ወንጀሎች መቆጣጠሪያ ቢሮ፣የውጭ ሀገር ስራና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ፌዴሬሽን እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት እንደሚይዝ ተደንግጓል፡፡

በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 7 የወንጀል መከላከልና የህግ ማስከበር የሥራ ቡድን አባላት በማዘርዘር ያስቀመጠ ሲሆን ይኸውም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሰብሳቢኔ የሚመሩ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሠላም ሚኒስቴር፣ የአፌዲሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የጉምሩክ ኮሚሽን፣ የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማእከል ፣የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ፣ የብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣የአፌዲሪ መከላከያ ሚኒስቴር፣ የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች አጀንሲ፣የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአደገኛ እጾችና ወንጀሎች መቆጣጠሪያ ቢሮ፣ የዓለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት እንዲያካትት ተደርጎ ተደንግጓል፡፡

በመመሪያው አንቀጽ 8 የተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የስራ ቡድን አባላት የዘረዘሩ ሲሆን በፌደራል ከተሞች ስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ሰብሳቢነት የሚመሩ የአፌዲሪ ግብርና ሚኒስቴር፣ የአፌዲሪ የሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር፣ የስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ፣ የአፌዲሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣የኢምግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲና፣የአፌዲሪ ጤና ሚኒስቴር፣ የአፌዲሪ ትራንስፖርት ሚኒስቴር፣የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር፣የፌደራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ማስፋፊያ ባለስልጣን፣፣የአፌዲሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣የፌደራል የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ/ኢንስቲትዩት፣የኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን፣የዓለም ዓቀፉ የፍልሰት ድርጅት፣የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአደገኛ እጾችና ወንጀሎች መቆጣጠሪያ ቢሮ፣ICRC፣አጋር ኢትዮጵያ፣የኢትዮጵያ አሰሪዎች ማኅበራት ፌዴሬሽን፣የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፣የሴቶች ሚዲያና ልማት ማህበር፣የዓለም የሥራ ድርጅት፣አፕሪፍስጉድ ሳሚቲታንና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት እንደያካትት ተደርጎ ተደንግጓል፡፡

ሌላው የሥራ ቡድን የዲያስፖራ ተሳትፎና ልማት ጉዳይ የሥራ ቡድን ሲሆን ኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ ሰብሳቢነት የሚመሩ የአፌዲሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣የኢትየጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣የአፌዲሪ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣የአፌዲሪ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ማህበር፣የአፌዲሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣የአፌዲሪ ጠቅላይ ዐ/ህግ፣የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ፣የአለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት፣የአለም ስራ ድርጅት እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን አንዲያካትት ተደርጎ በአንቀጽ 9 ተደንግጓል፡፡

የፍልሰት መረጃና አስተዳደር የሥራ ቡድን ሌላው የስራ ቡድን ሲሆን ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ የአፌዲሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣የአፌዲሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣የአፌዲሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣የአፌዲሪ ሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር፣የኢምግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች አጀንሲ፣የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ፣ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣የብሄራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን፣የአፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር፣የፌደራል ከተሞች ስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ፣የስደተኞችና ከፍልሰት ተመላሾች ጉዳይ አጀንሲ፣የዓለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት፣የፕላንና ልማት ኮሚሽን፣የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት በአባልነት እንደሚይዝ በአንቀጽ 10 ሥር ተደንግጓል፡፡

የሚቋቋሸው የሥራ ቡድን የጥናትና ምርምር የስራ ቡድን ሲሆን አንቀጽ 11 አንተማለከተው በኢፌዴሪ ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የሚሞራ ሆኖ የኢፌዴሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣የኢፌዴሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣የኢምግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች አጀንሲ፣ህግና ፍትህ ስልጠና ምርምር ተቋም፣የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኢንስቲቱት፣የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር፣አለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት፣የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአደገኛ እጾችና ወንጀሎች መቆጣጠሪያ ቢሮ፣ብሄራዊ ፕላን ኮሚሽን፣የአለም የስራ ድርጅት፣የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት ያካተተ ይሆናል፡፡

የመመሪያው ክፍል ሁለት) የትብብር ጥምረቱን የሥራ ቡድኖችን ዝርዝር ተግባርና አሰራር የሚደነግጉ ድጋጌዎችን የያዘ ሲሆን ከአንቀጽ 12-20 ያሉ 9 ድንጋጌዎችን የሚሸፍን ነው፡፡ አንቀጽ 12 ስለጠቅላላ የአሠራር ሥርዓት የሚደነግግ ሲሆን እያንዳንዱ የሥራ ቡድን እንደአስፈላጊነቱ በሥሩ ንዑስ ቡድኖችን ሊያደራጅ እንደሚችል ፣በስራ ቡድኖች ወስጥ የሚካተፉ ተቋማት ከሚሞለከታቸው የስራ ክፍሎች ተወካይ መመደብ እንዳለባቸዉና ተወካዮችም የስራ ክፍሉ ሀላፊዎች ወይም ምክትል ሃላፊዎች መሆን እንዳለባቸው፣ የስራ ቡድኖች የሚያቅደቿው እቅዶች እርበሳቸዉና ከትብብር ጥምረቱ ዕቅድ ጋር የተጣጣሙ መሆን እንዳለባቸው፣ የአባል ተቋማትን የሥራ ድርሻ በግልጽ ለይተው ማስቀመጥ እንዳለባቸው፣የተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎችን ልዩ ፍላጎት ባስገባ መልኩ ሥራቸዉን ማከናወን እንዳለባቸው፣ የስራ ቡድኖች እርስ በርሳቸው በቅንጅትና በትብብር ማስራት እንዳለባቸው እና ያንዳንዱ የስራ ቡድን ለትብብር ጥምረቱ ሰብሳቢ የአፈጻጸም ሪፖርት ማላክ እንዳለበት የሚደነግጉ ንዑስ ድንጋጌዎችን ይዟል፡፡

የመመሪያው አንቀጽ 13 የግንዛቤ ፈጠራና የባህሪይ ለወጥ እና የውጭ ሐገር ሥራ ሥምሪት የስራ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት በዝርዝር የያስቀመጡ 18 ነዑስ አንቀጾችን የያዘ ነው፡፡ በመሆኑም ወንጀሎቹን ለመካላከልና ተጋላጭነትን ለመቀነስ ይህ የሥራ ቡድን ስለፍልሰት በጎና አሉታዊ ጎኖች፣በሀገራችን ስላሉ አማራጭ የስራ ዕድሎች፣ ለወጭ ሀገር የሥራ ሥምሪት ያሉ ህጋዊ አማራጮች ለማህበረሰቡ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ መሥራት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ከዚህ በተጨማሪም የሀይማኖት አባቶችን እና የሚዲያ አካላትን በማስተባገር ለማህበረሰቡ የግንዛቤ ፈጠራ ስራ እንደሚሰራ፣ አዋጅ ቁጥር 923/2008 በትክክል ሥራ ላይ እንዲወል የመካታተል ኃላፊነት እንዳለበት እንዲሁም ከሌሎች የስራ የስራ ቡድኖች ጋር በቅንጅት መሥራት እንደላበት ይደነግጋል፡፡

ቀጣዩ የመመሪያው ድንጋጌ አንቀጽ 14 ሲሆን ስለወንጀል መካላከል እና የህግ ማስከበር የስራ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት የሚደነግግ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ድንጋጌ የወንጀል መካላከልና ህግ የማስከበር የሥራራ ቡድን ህብረተሰቡ በፍልሰት ዙሪያ ስለወጡ ህጎች ግንዛቤ እንዲኖረው ግንዛቤ የመፍጠር ሥራዎችን ከመሥራት ጀምሮ በህገወጥ መንገድ ድንበር የሚሸገሩ ዜጎችን የመመለስ፣ የድንበር ቁጥጥር ሥራዎችን በተቀናጀ መልኩ የማከናወን፣ በአጠቃላይ የህግ ማስከበር ተግባር የተሻለ እንዲሆን ከሚምለከተቻው አካላት ጋር በቅንጅትና በትብብር የመሥራት ኃላፊነት እንዳለበት በዝርዝር አስቀምጧል፡፡

በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 15 የተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የስራ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት በዝርዝር ያስቀመጠ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 1178/2012 ከያዛቸው ቁልፍ ጉዳዮች መካከል የተጎጂዎች ጥበቃና ድጋፍ አንዱ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የወንጀል ተጎጂዎች ከሚደርስባቸው አካላዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ኢኮኖሚዊና ሌሎች ጉዳቶች እንዲያገግሙ ለመልሶ ጥቃት እንዳይጋለጡ እንክብካቤና ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህን ተግባር እንዲወጣ የተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የስራ ቡድን ተደራጅቶ ዝርዝር ኃላፊነቱ በአንቀጽ 15 ሥር ባሉ 8 ንዑስ ድንጋጌዎች ተደንግጓል፡፡

በሌላ በኩል ፍልሰት በአግባቡ ከተመራ ለሀገራችን እንድገትና ልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው አከራካሪ አይሆንም፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ ወንጀሎችን ከመካላከል ጎን ለጎን የፍልሰተኞች አካል የሆነው የዳያስፖራ ማህበረሰብ ክፍል በሀገሩ ልማት እና ዕድገት የበኩሉን አበርክቶ እንዲያደርግ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ዓላማ በመነሳት በዚህ ረቂቅ መመሪያ የዳያስፖራ ተሳትፎና ልማት ጉዳይ የሥራ ቡድን እንዲደራጅ ተደርጎ ዝርዝር ተግባሩና አሠራሩ በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 16 ሥር ተደንግጓል፡፡

በፍልሰት ላይ የሚወሰን ማንኛወም ወሳኔ እና ወንጀሎቹን ለመካላከል እንዲሁም ተጎጂዎችን ለመደገፍ የሚወሰዱ ማንኛወም የፖሊሲ ፣ ስትራቴጂ፣ የህግ ዝግጅት እና ተግባራዊ እርምጃዎች በመረጃ ላይ የተመሰረቱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም ታማኒነት ያለው እና የተጣጣመ/ወጥ የሆነ ሀገራዊ መረጃ እንዲኖር በማሰብ የፍልሰት መረጃና አስተዳደር የሥራ ቡድን ተደራጅቶ ዝርዝር ተግባሩ በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 17 ሥር ተደንግጓል፡፡

የመጨረሻው የስራ በድን የጥናትና ምርምር የስራ ቡድን ሲሆን ለወንጀሎቹ መስፋፋት እና የዜጎች የተጋላጭነት ምክንያቶች በጥናት በመለየት ዘላቂ መፍትሄ ማስቀመጥና በተቀመጠው የመፍትሄ አቅጣጫ መሰረት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ምክንያት በረቂቅ መመሪያው የሥራ ቡድኑ እንዲደራጅ ሆኖ ዝርዝር ተግባሩ በአንቀጽ 18 ሥር ተደንግጓል፡፡

ሌላው በዚህ ረቂቅ መመሪያ የተሸፈነው የእያንዳንዱ የሥራ ቡድን ሰብሳቢ ስለሚኖረው ኃላፊነት ሲሆን በአንቀጽ 19 ሥር በዝርዝር ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት የሥራ ቡድን ሰብሳቢዎች የስራ ቡድኑን አባል ተቋማትን የማስተባበርና የመከታተል፣ መረጃዎችን የመያዝና ለትብበር ጥምረቱ ጽ/ቤት ዕቅድና ሪፖርት የመላክና ሌሎች ኃላፊነቶች አላቸው፤

በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 20 ላይ ስለትብበር ጥምረቱ መደበኛ የስብሰባ ጊዜ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም አስቸኳይ ስብሰባ ሊያስፈልግ የሚችል መሆኑ እንዳለ ሆኖ ጥምረቱ በየሩብ አመቱ እና እያንዳንዱ የሥራ ቡድን ደግሞ በየሁለት ወሩ እንደሚሰበሰብ ተደንግጓል፡፡

በመጨረሻም የረቂቅ መመሪያው ክፍል ሦስት ልዩ ድንጋጌዎች እንዲይዝ ተደረጎ የተቀረጸ ሲሆን በወስጡም ማንኛወም አካል መመሪያውን ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ እንዳለበት( አንቀጽ 21)፣ መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ( አንቀጽ 22) እና መመሪያ ተፈጻሚ መሆን የሚጀምርበትን ጊዜ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ይሸፍናል፡፡